# “ወዘመዉ በጣዖቶሙ”
# (በጣዖታቸው ሰሰኑ)

ከሊ. ማ. አበባው ይግዛው

በቦሌ መድኃኔዓለም ቤተ-ክርስቲያን ተተከለ ሥለተባለው የአባ ጳውሎስ ሐውልት እኔም ትንሽ የምለው አለኝ።

ከካቶሊካዊት ቤተ-ክርስቲያን በስተቀር የኦርቶዶክስ አብያተ-ክርስቲያናት በሙሉ፣ በግርግዳ፣ በሰሌዳም ሆነ በንዋያተ-ቅድሳት ላይ የሚዳሰስና የተቀረጸ ምስል አያስቀምጡም። ይህም ሥርዓት በቀኖና የጸደቀ፣ በሕገ-አምልኮ ለዘመናት የተጠበቀ ነው። የኢትዮጵያም ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን የኦርቶዶክሳውያኑ እህትና አጋር እንደመሆኗ ይህን የተቀደሰ ሥርዓት ጠብቃ ኖራለች። በቤተ-ክርስቲያን ውስጥም ሆነ በቅጽረ-ቤተክርስቲያን የማንንም ሐውልት አታስቀምጥም። ደግ የሰሩ የቤተ-ክርስቲያን አባቶችም ሆኑ ምዕመናን ካሉ ስዕላቸው በተማሕጽኖ መልክ ይሣላል።

አብርሃም አባታችን ይረዳሃል የተባለውን ግዑዝ ጣዖትን ሰብሮ፣ ተራራን ዞሮ፣ ወንዝን ተሻግሮ፣ ተራራውን ንፋሱ ሲጋርደው አይቶ በተራራው፣ ተራራውን ወንዙ ሲጎርደው አይቶ በወንዝ፣ ወንዙን ፀሐይ ሲያደርቀው ተመልክቶ “አምላከ - ፀሐይ ተናበበኒ።” ብሎ ቀጥተኛ ሃይማኖቱን ያገኘና በዘሩ የተባረከ አንደሆነ መጻሕፍት ይነግሩናል፤ አባቶች ያስተምሩናል።

አብርሃም ጣዖትን ሰባብሮ ነፃ ያወጣትን እምነት ደላሎች በዘመናችን በአምልኮ-ባዕድ ሲበክሉዋት ማየት ከባድ ሀጢአት ነው። የአባ ጳውሎስ ሐውልትም በቅጽረ-ቤተክርስቲያን መተከል መልኩንና ዘመኑን የለወጠ አምልኮ-ባዕድ ነው። በፈቃዳቸው ይደረግ አይደረግ አላውቅም። ተባርኮ መመረቁን ግን የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አረጋግጠዋል። መስቀልና አርዌ-ብርት የያዘ ጣዖት በደመቀ ስዕል ይታያል። የነገረ-መለኮት ዶክተር ነኝ እንደማለታቸው ይህ ከባድ ስሕተት ሥለሆነ መከልከል ነበረባቸው። ሐውልቱ ቤተ-ክርስቲያኑንም ሆነ እርሳቸውን ያዋርዳል እንጂ አያስከብርም። በግድ ይሁን ከተባለ እንኳዋ ከአሰሩት የመኖሪያ ቤታቸው ላይ ቢሰቅሉት ይመረጣል።




ይህ አሳፋሪ ተግባር በሲኖዶስም ሆነ በካህናትና ምዕመናን ሊወገዝ ይገባዋል። የካቶሊክ ባህል በየጊዜው በስዕሉም፣ በመስቀሉም፣ በሐውልቱም፣ በንዋየ-ቅድሳቱም እየሠረገ ሲገባ እንደዋዛ መመልከት ኦርቶዶክሳዊነት አይደለም። የኦርቶዶክስ ልጆች እንደጀመሩት በእንጭጩ ሊቀጩት ይገባል። ሰው የሠራውን ሰው ያፈርሠዋል። ለዚህ ይሉኝታ አያስፈልግም።

ለዝክረ-ታሪክ እንዲሆን አባባሌን እንደ አባቶች በቅኔ ለመግለጽና የእርኩሰቱን ፈፃሚዎች መገሠጽ

እፈልጋለሁ። አሁንስ ከትዕግሥት በላይ ሁነዋል።

<u>ጉባኤ ቃና 1</u>

ስብኮ ግዑዝ እንተ አብርሃም ደምሰሶ፣
በቦሌ ተንሥአ ሥጋ ጳውሎስ ለቢሶ።

<u>ትርጉም</u>

አብርሃም (ጥንት) የሰባበረው ግዑዝ ጣዖት፣
(በዘመናችን) የጳውሎስን ሥጋ ለብሶ በቦሌ ተነሳ።

<u>ጉባኤ ቃና 2</u>

ይቤ ዳዊት ለዘአእዛኒሆን አርኃው፣
እለጌታቸው ነደቅት በጣዖቶሙ ዘመዉ።

<u>ትርጉም</u>

ጆሮአቸውን ከፍተው ለሚያዳምጡ ሁሉ፣ ዳዊት እንዲህ ይላል፣
ጣዖት ሰሪዎች እነጌታቸውና ግብረ-አበሮቻቸው በጣዖታቸው ሰሰኑ (ቀነዘሩ)።

ዝሙት በሴትና በወንድ ፍቅር ብቻ የተወሰነ አይደለም። ፍቅረ-ሥልጣን፣ ፍቅረ-ንዋይም ሆነ ፍቅረ-ጣዖት (አምልኮ-ባዕድ) ከባድ ዝሙት ነው። ለዚህ ነው ነቢዩ "ወረኩሱ በንግባሪሆሙ፤ ወዘመዉ በጣዖቶሙ።" (በምግባራቸው ረከሱ፤ በጣዖታቸው አመነዘሩ።) ያለው። (መዝሙር 105፣ ቁ 39) ስለሆነም ጣዖት የሚቀርጹ፣ ጣዖት የሚያስቀርጹና ለጣዖት የሚሰግዱ ሁሉ ዘማውያን ናቸው። ከማህበር መወገድ አለባቸው።

"ያሕዛብ ጣዖታት፣ የወርቅና የብር የእጅ ሥራ ናቸው። አፍ አላቸው አይናገሩም፤ ዓይን አላቸው አያዩም፤ ጆሮ አላቸው አይሰሙም፤ አፍንጫ አላቸው አያሸቱም። እጅ አላቸው አይዳስሱም፤ እግር አላቸው አይሄዱም፤ በጉሮሮዋቸውም አይናገሩም። የሚሰርዋቸውም የሚያምኑባቸውም ሁሉ እንደ እነሱ ይሁኑ።"

(መዝሙረ ዳዊት 115፣ ከቁ. 12 እስከ 17)

ቤተ-ክርስቲያንን ባለቤቷ ይጠብቃት።

(ሐምሌ 2002 ዓ. ም.፣ ለንደን)